# ደምብ/ሥርዓት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

**ተዛማጅ ግብአቶች፡-** BBB, EDC, EDC-RA, EGI-RA, EHC-RA, IGS, JFA, JFA-RA, JHF-RA, JOA-RA, KBA-RB, KBB
**ኃላፊነቱ የሚመለከተው ጽ/ቤት፡-** የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

## ስለ ኮምፒውተር ሲስተሞች፣ ስለ ኤሌክትሮኒክ መረጃዎች እና ስለ አውታረ መረብ ደህንነት የተጠቃሚ ኃላፊነቶች

I. **ዓላማ**

A. ሁሉንም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኮምፒውተር ሲስተሞችን መሠረታዊ ነገሮች፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂ፣ እና የኤሌክትሮኒክ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ደህንነት ለማረጋገጥ፣

B. የ MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞችን ለሚጠቀሙ ሁሉ አግባብ የሆነ አጠቃቀምን በዝርዝር ለመግለጽ/ለማብራራት፤

C. የኮምፒውተር ሲስተሞችን፣ ተዛማጅ ቴክኖሎጂ፣ እና ኤሌክትሮኒክ መረጃ-ኢንፎርሜሽን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በመጠቀም የአእምሮ እውቀትን ለማጎልበት፣ እና

D. አግባብነት ካላቸው የስቴት፣ የአካባቢ፣ እና የፌደራል ህጎች ጋር ስሙሙ መሆኑን ለማረጋገጥ።

II. **የበፊት ታሪክ**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኮምፒውተር ኢኩፐመንት፣ የኮምፒውተር አገልግሎቶችን፣ እና የአውታረመረብ ተደራሽነትን ለትምህርት ቤቶች እና ለቢሮዎች የሚሰጠው ከ MCPS ተልእኮ ጋር ለሚጣጣሙ ዓላማዎች ነው። ለ MCPS ተጠቃሚዎች ያለው ባለ ብዙ ፈርጅ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አዳዲስ ስጋቶች እና እድሎችም አሉት። ተገቢ የሆነ ስነምግባርን የመጠበቅ-የማክበር ሀላፊነቱ የሁሉም የ MCPS ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መገልገያዎች እና የኮምፒውተር ፋሲሊቲዎች ተጠቃሚ ግለሰቦች ይሆናል። በትምህርት ቤቶች፣ የወጣቶች/minors ኦንላይን አክቲቪቲዎች አጠቃቀም በሠራተኞች እና በሲስተም አቀፍ የቴክኖሎጂ ጥበቃ ዘዴዎች ቁጥጥር ይደረጋል። የተደራሽነቱ ደረጃ የሚሰጠው በሚሠራው ሥራ/assignment፣ ኃላፊነት፣ እና ከማወቅ ፍላጎት ጋር እየተመዛዘነ ይሆናል። ተጠቃሚዎች መረጃዎችን እና ሪሶርሶችን ከስርቆት፣ ጥላቻን ያዘለ ጉዳት-ብልሽት፣ ካልተፈቀደ ተጠቃሚነት፣ ከአሣሳች ጣልቃ ገብነት፣ እና ከጥፋት መጠበቅ/መከላከል አለባቸው።

III. **ትርጉም**

A. approved electronic signature method/የፀደቀ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ዘዴ ማለት በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና/ወይም በተወካይ የፀደቀ/የተፈቀደ፣ በዚህ ድንጋጌ እና ጠቅላላ በተግባር ላይ የዋሉ የስቴት እና የፌደራል ህጎች መሠረት፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማዎችን አይነት ለይተው የሚያሳዩ፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አጠቃቀምን ሲስተም እና ሂደት፣ እና የኤሌክትሮኒክ ፊርማን ጠቀሜታ የሚያሳይ ነው።

B. የኮምፒውተር ሲስተም ሃርድዌር፣ ሶፍትዌር/ hardware፣ software፣ እና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ፣ አውታረመረቦችን ጭምር፣ የጽሑፍ፣ እና የኮሙኒኬሽን መሳሪያ/equipment ማለት ነው።

C. በሳይበር ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ እና/ወይም በኤሌክትሮኒክስ ደጋግሞ ማስጨነቅ ወይም ማስፈራራት/Cyberbullying and/or electronic harassment or intimidation ማለት ሆን ተብሎ የሚደረግ በኢ-ሜይል፣ በፈጣን አጫጭር መልእክቶች፣ በማህበራዊ ገጾች፣ በብሎግስ፣ በሞባይል ስልኮች፣ ወይም በሌላ የቴክኖሎጂ ዘዴዎች የተማሪን የትምህርት ጥቅሞች፣ ዕድሎች፣ ወይም የስራ አፈፃፀም፣ ወይም በተማሪ አካላዊ ወይም ሥነ ልቦናዊ ደህንነት በከፍተኛ ሁኔታ ጣልቃ በመግባት የማይመች/ተጻራሪ የሆነ የትምህርት አካባቢ መፍጠር፣ እናም:-

- በዘር፣ ብሔራዊ ማንነት፣ የጋብቻ አቋም፣ ጾታ፣ የጾታ መገለጫ፣ የጾታ ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የዘር አመጣጥ፣ አካላዊ ባህርይ፣ ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ አቋም፣ ቤተሰባዊ አቋም፣ ወይም አካላዊ ወይም አእምሮአዊ ችሎታ ወይም ስንክልናን ያካተተ ባህሪያት በተጨባጭ ወይም በይሆናል ግላዊ አስተሳሰብ በመገፋፋት

- ዛቻ ወይም አደገኛ ማስፈራራት

- በትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ወይም ሁነት ላይ፣ ወይም በትምህርት ቤት አውቶቡስ ዉስጥ የሚከናወን

- በሥርዓት እየተካሄደ ያለውን የትምህርት ቤት ሥራን በከባድ ሁኔታ ያደናቅፋል

D. ትምህርታዊ ዓላማዎች/Educational purposesማለት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)ን ትምህርታዊ፣ የማስተማር፣ አስተዳደራዊ፣ የቢዝነስ፣ እና ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶችን ተልእኮ እና ከማንኛውም የማስተማር ተግባር ጋር የተገናኘ፣ ፕሮጀክት፣ ሥራ፣ የሚተገበር ነገር፣ ወይም በተጠቃሚው(ዋ) ኃላፊነት የሚከናወኑ ነገሮች ማለት ነው።

E. የኤለክትሮኒክ ዳታ እና መረጃ-ኢንፎርሜሽን/Electronic data and information ማለት በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ ወይም ዲጅታል ቅርፅ የሚገኙ ጭብጦች/መረጃዎች ወይም ቁጥሮች/ቅርጾች ማለት ነው። ምሳሌዎቹ የሚያካትቱት:- ኢ-ሜይል፣ አጫጭር ፈጣን መልእክቶች፣ የጽሑፍ ንግግር አውዶች፣ ቴክስቶች-አጫጭር የጽሑፍ ምልልሶች/ቴክስቶች፣ ዶኩመንቶች፣ የመረጃ ቋቶች፣ ፋይሎች፣ ድረ-ገጾች፣ እና ማናቸውም በኤሌክትሮኒክ የሚከማቹ ሌሎች መረጃዎች ናቸው።

F. የኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ/electronic record ማለት ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ/ቢዝነስ ትግበራ ጋር የተገናኘ፣ ከሥራ አጋሮች-ሽሪኮች ጋር የተደረጉ የግንኙነት ልውውጦች መረጃዎች፣ እና ለ MCPS በማስረጃነት የተቀመጡ ዶኩመንቶች በዲጅታል ቅርፅ የተሠሩ፣ የተላኩ፣ የተገኙ፣ ወይም በዲጅታል ቅርጽ የተከማቹ ናቸው። ሪኮርድ የተባለው መረጃ/ኢንፎርሜሽን ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚቆዩ/አላፊ ባህርይ ያላቸውን ለወትሮ የማይቆዩ አይነት ሪኮርዶችን አይጨምርም።

G. የኤሌክትሮኒክ ፊርማ/electronic signature ማለት በሪኮርድ ፈራሚው(ዋ) ሰው አማካይነት ገቢራዊ/በተገቢ አስተሳሰብ ከኤሌክትሮኒክ ሪኮርድ ጋር የተገናኘ እና የሚሠራ ወይም በሥራ ላይ የዋለ ኤሌክትሮኒክ ድምፅ፣ ቅርጽ/ምልክት፣ ወይም አሰራር ነው።

H. ተገቢነት የሌላቸው ቁሳቁሶች-ማቴሪያሎች/Inappropriate materials ማለት በዚህ ደንብ ላይ በተገለጸው አይነት ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፖሊሲዎች እና ደንቦች መሠረት ትምህርታዊ ዓላማ የሌላቸው ቁሳቁሶች እና በልጆች/በተማሪዎች ላይ ጉዳትን የሚያስከትሉ ፀያፍ፣ ስድ፣ ወይም ወሲባዊ ስሜትን የሚቀሰቅሱ፣ ቅንዝረኛ-ጠንካራ የወሲብ ፍላጎትን የማነሳሳት ይዘት ያላቸው የአዋቂዎች፣ የኅልማሶች ድረገጾችን ጨምሮ፣ ትምህርታዊ ዓላማ የሌላቸው እድሜን የማይመጥኑ ቁሳቁሶች ናቸው። ተገቢ ያልሆኑ ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች በተጨማሪ የሚያካትቱት ያለፍቃድ የኮምፒውተርን ሥርዓት

በመጣስ መረጃ መበርበር፣ እፆችን፣ አልኮል፣ እና ትምባሆ መጠቀም፣ ማሠራጨት፣ እና የማምረት-ማራባት፣ ዛቻ፣ ማስፈራራያ፣ ማስጨነቅ፣ የወንጀል ድርጊቶች፣ ሁከት ወይም በህገወጥነት የጦር መሣሪያ መጠቀም ወይም መያዝ። እውነተኛ መሆኑን ማረጋገጫ ማስረጃ ሲፈለግ ወይም ለሌላ ህጋዊ ዓላማ በሠራተኛ ከተፈለገ፣ በተገቢ ሁኔታ እንዲመለከቱ ሊፈቀድ ይችላል።

I. ኢንተርኔት ማግኘት/Internet access በጠቅላላ ከኢንተርኔት አገልግሎት ጋር እና ከተጠቃሚዎች ጋር የተፈቀዱ ዘዴዎችን መጠቀም፣ እና ተደራሽነትን ለመስጠት በጠቅላላ የተፈቀዱ ዘዴዎችን ይጨምራል።

J. የ የቴክኖሎጂ ደህንነት የመጠበቅ እርምጃ/technology protection measure ማለት ተገቢነት የሌላቸውን ቁሳቁሶች-ማቴሪያሎች ተደራሽነት ለመከላከል ወይም ለመገደብ በተነደፈ ዓላማ የተለየ መስፈርት በማዘጋጀት የተመረጡ የኢንተርኔት ክፍሎችን/portions የማጣራት ቴክኖሎጂ ነው።

K. ያልተፈቀደ መሣሪያ/Unauthorized equipment ማለት በ "Office of the Chief Technology Officer (OCTO)" አማካይነት እና/ወይም በእርሱ/ሷ ተወካይ አማካይነት ከ MCPS ኮምፒውተር ጋር ወይም የ MCPS ኔትዎርክ ጋር እንዲገናኝ ያልተፈቀደ፣ ነገር ግን በዚህ የተገደበ ባይሆንም፣ ከኮምፒውተሮች ጋር፣ ታብሌት ዲቫይሶች፣ የግል መገናኛ እና የድርጅት ዲቫይሶችን "wireless access points/መስመር አልባ መገኛ ነጥቦች፣ smart phones/ስማርት ስልኮች፣ወይም cell phones/ሞባይል ስልኮች፤የጌም መጫወቻ መሳሪያዎች/gaming devices፤ የፎተግራፍ መሳሪያ/photographic equipment፤እና የመዝናኛ መሳሪያዎች/entertainment devices such as MP3 players or iPods™" ሁሉ ያካትታል።

L. ተጠቃሚ/userማለት ማንኛውም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሥራ ባልደረባ፣ ተማሪ፣ ወይም የ MCPS ኮምፒውተር ለመጠቀም የተፈቀደለ(ላ)ት ሌላ ግለሰብ ማለት ነው። ሌሎች ግለሰቦች ማለት ወላጆችን፣ በጎፈቃደኞችን፣ እና ኮንትራክተር ወይም ጊዜያዊ ሠራተኛን ሊያካትት ይችላል።

## IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

ስለ ኤሌክትሮኒክ ዳታ እና የመረጃ/ኢንፎርሜሽን ደህንነት፣ በኤሌክትሮኒክ የሚከናወኑ ልውውጦች እና ፊርማዎች ፊዚካል ደህንነት፣ የሲስተም እና አፕሊኬሽኖች ደህንነት፣ የመገናኛ አውታረመረብ ደህንነት፣ እና cybersafety፣ cybersecurity፣ እና cyberethics፣ አስፈላጊ የአሠራር ሥርዓቶችን-መሥሪያ መንገዶች- በሚከተለው ክፍል በዝርዝር ተብራርቷል-ተገልጿል። ስለ ኮምፒውተር ሲስተሞች ደህንነት የተጠቃሚ ኃላፊነትና ዝርዝር የአጠቃቀም ሥርዓት Manual of MCPS Computer Systems Security Procedures በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

A. የኤሌክትሮኒክ ዳታ እና የኢንፎርሜሽን ደህንነት/Electronic Data and Information Security

ተጠቃሚዎች ለመረጃ እና/ወይም ለኮምፒውተር ሲስተም መዳረሻ የሚኖራቸዉ ለተፈቀደላቸው እና ለሚያስፈልጋቸዉ ሥራዎች እና ኃላፊነቶች ብቻ ነው።

1. ተጠቃሚዎች ስለራሳቸው አካውንት ሃላፊነት አለባቸው።

    a) ተጠቃሚዎች እንደአስፈላጊነቱ ይለፍ ቃልን/passwords መቀየር አለባቸው እና ይለፍ ቃሎችን/passwords በከፍተኛ ጥንቃቄ በምስጢር መጠበቅ አለባቸው።

    b) ተጠቃሚዎች አካውንታቸውን እና የይለፍ ቃልን/passwords ለሌላ ሰው መስጠት፣ማሳየት፣ማስተላለፍ በጥብቅ የተከለከለ ነው።

    c) ከግል አካውንት ስም ጋር የተያያዙ ማንኛውም ጥሰቶች የአካውንቱ ባለቤት ሃላፊነት ተደርጎ ይወሰዳል።

2. ተጠቃሚዎች ኮምፒውተራቸውን ለቀው ከመነሣታቸው በፊት፣ ከሥራ ቦታቸው ከመነሳታቸው አስቀድመው፣ ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙበት ከመፍቀዳቸው በፊት በጥቅላላ ሲስተሞቹን መዝጋት/log off ማድረግ አለባቸው።

3. በዚህ ደንብ መሠረት ግንዛቤ መውሰድ እና የደህንነት መስፈርቶችን መከተል የሁሉም ተጠቃሚ ኃላፊነት ነው።

4. ተጠቃሚዎች የራሳቸውን የኤሌክትሮኒክ ዳታ በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው። (ማስታወሻ፦ እንዳይጋለጡ በጥንቃቄ መያዝ ያለባቸው ፋይሎች መቀመጥ ያለባቸው በግል የኔትዎርክ ፋይል ላይ/ወይም በፋይል ማከማቻ ሣጥን ነጥሎ ማስቀመጥና መቆለፍ በሚቻል ዲስክ ላይ/individual's network folder/directory or a removable disk that is then secured in a locked file cabinet በመሣሰለ ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ ሥፍራ ነው።)

5. በሲስተም ብልሽት ወይም በመጨናነፍ ምክንያት ለሚያጋጥም የኢንፎርሜሽን መጥፋት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ኃላፊነት የለበትም። ተጠቃሚዎች መጠባበቂያ ቅጅዎችን መያዝ እና ደህንነቱ አስተማማኝ በሆነ ሥፍራ መቀመጡን ማረጋገጥ አለባቸው።

B. በኤሌክትሮኒክ ክንውን ሂደቶች እና ፊርማዎች

የሜሪላንድ ስቴት ህግ፣ የፌደራል ህግ፣ ወይም የ MCPS ፖሊሲዎች እና ደንቦች ግብይይት ህጋዊነት ያለው ሰው ፊርማ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ የተፈቀደ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ዘዴ በመጠቀም የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ከተፈረመበት መስፈርቱ የተሟላ ይሆናል። የኤሌክትሮኒክ አጠቃቀም አሠራር እና ፊርማ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርአት በManual of the MCPS Computer Systems Security Procedures/የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞች ደህንነት የአሰራር ሥርአት መምሪያ መፅሀፍ ተገልጿል።

C. የቁሳቁስ አካላዊ-ፊዚካል ደህንነት/Physical Security

የኮምፒውተር ሲስተሞች መሣሪያ ደህንነታቸው በተጠበቀ አካባቢ መቀመጥ እና መጠበቅ አለባቸው። ተጠቃሚዎች የኮምፒውተሮች እና ተዛማጅ ቴክኖሎጂ አካላዊ-ፊዚካል ደህንነት አጠባበቅ ደንቦችን የመከተል ሃላፊነት አለባቸው።

1. አካባቢውን ለመቆጣጠር የሥራ ባልደረቦች በማይኖሩበት ወቅት፣ ሁሉም አካባቢ (ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ማስቀመጫ ቦታዎች) ዋጋ ያለው የኮምፒተር እቃ በማያሳስብ አስተማማኝ ሁኔታ መጠበቅ አለበት።

2. ኮምፒውተር ወይም ተዛማጅ መሣሪያ/equipment በአግባቡ ካልተፈቀደ በስተቀር ከ MCPS ንብረት መወገድ አይኖርባቸውም።

3. ማንኛውንም ኮምፒውተር ወይም ተዛማጅ መሣሪያ/equipment ለመክፈት ወይም ለመዝጋት- sign in or out ተጠቃሚዎች በቦታው የተጠያቂነት ሥርዓት መዘርጋት አለባቸው። ተጠቃሚው(ዋ) MCPS ን ከመልቀቁ(ቋ) በፊት ወይም ወደ ሌላ ትምህርት ቤት ወይም ጽ/ቤት ከመዛወሩ(ሯ) አስቀድሞ ይህ እቃ ወደ ትምህርት ቤት፣ ዲፓርትመንት፣ ዋና ክፍል፣ ወይም ን/ክፍል መመለስ ይኖርበታል።

4. የቦታው የእቃ/equipment ዝርዝር ቆጠራ-ቁጥጥር በተቻለ መጠን በትክክል ይጠበቃል። መሣሪያዎች-Equipment ሲገኙ-ሲገዙ በቆጠራው ዝርዝር ላይ ይጨመራሉ። ተጠቃሚዎች

የቆጠራ/inventory ምልክቶችን የዝርዝር መለያ ወይም ታጎችን-tags ከኮምፒውተሮች ላይ ማንሳት-ማስወገድ አይኖርባቸውም።

5. የጠፋ ወይም የተሠረቀ እቃ ቁጥጥር መደረግ ያለበት በ MCPS Regulation EDC-RA መሠረት ነው፣Control of Furniture and Equipment Inventory/የቢሮ እቃዎች ቁጥጥር እና የእቃዎች ዝርዝር።

D. የሲስተም እና የመተግበሪያዎች ደህንነት/Systems and Applications Security

1. ተጠቃሚዎች ሶፍትዌር-software ወይም ሃርድዌር-hardware ለአገልግሎት ማዘጋጀት የለባቸውም፣ ወይም በማንኛውም ኮምፒውተር ወይም ሌላ ህጋዊ የዲጅታል/ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ላይ ለደህንነት የተቀመጡ ነገሮች ላይ (የፀረ ቫይረስ ሶፍትዌር የመሣሰሉትን) ኃላፊነቱ ከሚመለከተው ሠራተኛ ፈቃድ ሳይሰጥ በማንኛውም ምክንያት፣ በ Manual of MCPS Computer Systems Security Procedures/የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞች ደህንነት የአሰራር ሥርአት መምሪያ መፅሀፍላይ እንደተገለጸው ለውጥ ማድረግ የለባቸዉም።

2. ተጠቃሚዎች በ--ላይ እንደተገለጸው፣ አግባብነት ካለው ሠራተኛ ፈቃድ ሳይሰጥ የሲስተሙን የተገጠሙበትን አኳኋን-አሠራሮች-settings መቀየር የለባቸውም Manual of MCPS Computer Systems Security Procedures/የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞች ደህንነት የአሰራር ሥርአት መምሪያ መፅሀፍ።

3. የ MCPS ሶፍትዌር እና መተግበሪያዎች/applications በፈቃድ መስጫ ስምምነቱ ላይ ከተገለጸው ሁኔታ በስቀር የ MCPS ባልሆኑ ኮምፒውተሮች ላይ መጫን ወይም መገልበጥ የለባቸውም።

E. የአውታረመረብ ደህንነት/Network Security

በጠቅላላ በ MCPS ኔትዎርክ እና ኢንፎርሜሽን ለመጠቀም ኃላፊነት በተሰጠው የ MCPS ባለሥልጣን በ OCTO መፈቀድ-መፅደቅ አለበት። ይህንን ወይም ሌላ የ MCPS ፖሊሲ ወይም ደንብ በሚጥስ ሁኔታ የአውታረመረብ-network ወይም የመረጃ አጠቃቀም መፈጸሙ ከተረጋገጠ፣ የተጠቃሚው(ዋ) አካውንት ወይም ከተጠቃሚነት ሊወገድ፣ ሊታገድ፣ ወይም ሊከለከል ይችላል።

F. ስነምግባር እና አጠቃቀም/Conduct and Use

የተማሪ እና የሠራተኛ የኢንተርኔት አጠቃቀም በዚህ ባይወሰንም፣ በተለያዩ ዘዴዎች፣ በቴክኖሎጂ እና በቀጥታ ቁጥጥር ይደረጋል።

1. በኔትዎርክ አማካይነት ተደራሽነት ያላቸው ነገሮችን ወይም ማቴሪያሎችን ማምጣት-ማስገባት በዚህ ደንብ መሠረት ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ መሆኑን ማረጋገጥ የተጠቃሚዎች ሃላፊነት ነው።

2. በዚህ ደንብ ላይ በተገለጸው መሠረት፣ ማንኛውም ማቴሪያል ወይም መረጃ ሆነ ተብሎ ፖስት የተደረገ ወይም ከ MCPS ሲስተም ጋር ወይም ከኢንተርኔት ጋር የተገናኘ ከሆነ፣ ከትምህርታዊ ዓላማ ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት።

3. ተጠቃሚዎች ለሚገለገሉባቸው እና በ MCPS መሣሪያ/equipment በኢንተርኔት አማካይነት ለሚያገኟቸው ጭምር ለኮምፒውተር ሲስተም(ሞች) የተዘጋጁ የሚተገበሩ ህጎችን የማክበር ኃላፊነት አለባቸው።

4. ከሌሎች ሲስተሞች ወይም ኢንተርኔት በ MCPS አማካይነት ለሚያገኟቸው የኢንተርኔት መደቦች/sites መረጃዎች-ኢንፎርሜሽን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ መቆጣጠር አይችልም እና ሃላፊነትም መውሰድ አይችልም። አንዳንዶቹ ከ MCPS ውጪ የሚገኙ ምንጮች/sites እና ሲስተሞች ስም የሚያጠፉ-የሚያጎድፉ፣ ትክክል ያልሆኑ፣ የስድብ-የሰውን ክብር የሚነኩ፣ አስፀያፊ-ነውረኛ፣ ክብር የማይሰጥ-የንቀት፣ ወሲባዊ ነገር ላይ ያተኮረ፣ ዛቻ፣ ዘረኝነት የተሞላበት፣ ወይም ህገወጥ ማቴሪያል ሊሆን ይችላል።

5. በሰክሽን "Section III.D" እንደተገለጸው በጠቅላላ የኮምፒውተር ፋሲሊቲዎችን፣ ኔትዎርክ፣ ሌሎች የቴክኖሎጂ ሪሶርሶችን መጠቀም፣ ለትምህርታዊ ዓላማ ብቻ መሆን አለበት፣ እና MCPS ለመገምገም እና ተያይዞ ሊቀመጥ ይችላል።

6. የ MCPS ኢ-ሜይል ለትምህርት ዓላማ ብቻ ነው/MCPS e-mail is for educational purposes only። ሁሉም እንቅስቃሴዎች/ተግባሮች MCPS ሊቆጣጣራቸው ይችላል ታይተውም ሊመዘገቡ (logged) ይችላሉ። የ MCPS ን ኢ-ሜይል ተጠቃሚ ተማሪዎች በሙሉ መፈቀድ ያለበት የትምህርት ሒደትን ለመደገፍ ወይም ለማመቻቸት ዓላማዎች ብቻ ነው።

7. ለተማሪዎች --መጠቀም የተከለከለ ነው-ያልተፈቀደ/unauthorized ኢ-ሜይል/e-mail፣ አጫጭር ፈጣን መልእክቶች/instant messaging፣ ወይም የውይይት ክፍሎች/chat rooms።

8. ተገቢ ያልሆኑ የኮምፒውተር ፋሲሊቲዎችን አጠቃቀም እና ባህርይ በሙሉ መመዝገብ-በዶኩመንት መያዝ የማይቻል ቢሆንም፣ የሚከተሉት መመሪያዎች ስለተከለከሉ የኮምፒውተር እና የኔትዎርክ አጠቃቀም ደንብ/ህግ መጣስ ምሳሌዎችን ያመለክታሉ፦

    a) ሲስተም መቀየር፣ ማሳሳት፣ ጣልቃ መግባት (ያለፈቃድ የኮምፒውተርን ሥርአት በመሰርሰር መረጃ መበርበር በመባልም ይታወቃል) ወይም በማንኛውም የ MCPS ሲስተም መመሪያዎችን ወይም ኢንፎርሜሽን በመስጠት መረጃ ለመበርበር ሌሎችን መርዳት፣ (ማናቸውም የሚሠሩ ሲስተሞችን፣ የግል አካውንቶችን፣ ኔትዎርክ ማከፋፈያ ፎልደርን፣ ሶፍትዌር፣ አውታረመረብ ፋሲሊቲዎች፣ እና/ወይም ሌሎች ፕሮግራሞችን ያልተፈቀደ ለውጥ ማድረግ) እና/ወይም እቃ-equipment ማበላሸት።

    b) በኮድ የተጻፈውን ወደ መደበኛ ቋንቋ መለወጥ፣ መነጠ-ቁልፍ/key logging፣ ወይም ያለፈቃድ ሃርድዌሮችን ወይም ሶፍትዌር መተግበሪያዎችን በመጠቀም ይለፍ ቃሎችን መጥለፍ፣ እና/ወይም ያለፈቃድ የከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚነት/ልዩ ተጠቃሚነትን ማግኘት ወይም ለማድረግ መሞከር።

    c) በሌሎች የኔትዎርክ ተጠቃሚዎች መገልገያ፣ ወይም በኮምፒውተር አጠቃቀም ጣልቃ መግባት፣ እንደ አገልግሎት መከልከል የሙሣሉ-denial of service (DoS) ወይም አገልግሎት እንዳይሰጥ የተደረገ ስርጭት distributed denial of service (DDoS) ሆን ብሎ መፈጸም።

    d) ስም ማጥፋት-libelous፣ በሀሰት ስም ማጉደፍ-slanderous፣ በኮምፒውተር ወይም በኤሌክትሮኒክ ማጥቃት-cyberbullying፣ መነዝነዝ-harassment፣ ወይም በሌሎች ላይ መዛት፣ ማስፈራራት-intimidation የሙሣሰሉ መግለጫዎችን ወይም ተግባሮችን መፈጸም።

e) በ III ላይ እንደተገለጸው አይነት ሆን ተብሎ-እየታወቀ የሚደረግ አግባብነት የሌለው ቁሳቁስ/material መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር። H. ከላይ/above

f) የ MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞችንና የታሰቡ ሥራዎችን በተንኮል-የሚጎዳ ኮዶችን/ሶፍትዌር እንደ ቫይረስ ወይም ዎርምስ የመሣሠለ የሚጎዳ ወይም የሚደመሥስ ነገርን ማስተዋወቅ-መጠቀም።

g) ያልተፈቀደ መሣሪያ/equipment ከማንኛውም የ MCPS ኮምፒውተር ጋር ወይም የ MCPS አውታረመረብ/network ጋር የ OCTO እና/ወይም የእርሱ(ሷ) ተወካይ ፈቃድ ሳይኖር ማያያዝ-ማገናኘት።

h) ኢ-ሜይል በመጠቀም ሌሎችን ማስፈራራት ወይም ማታለል፣ ማጭበርበር ዛቻ ወይም ማስፈራሪያ በመላክ ወይም ያልተገባ በርካታ እና/ወይም የንግድ መልእክቶችን በኢንተርኔት መላክ፣ ወይም የማንነትን መለያ ለመስረቅ የተጭበረበረ የኢ-ሜይል መልእክቶችን በመጠቀም የግል መረጃ-ኢንፎርሜሽን ማግኘት።

i) ውክልናን፣ መተግበሪያዎችን፣ ወይም ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የቴክኖሎጂ መከላከያ-መጠበቂያ፣ በአንጻሩ የኔትዎርክ ደህንነት ወይም የቴክኖሎጂ ማጣሪያ ተብለው የሚታወቁ ዘዴዎችን በዘዴ ማክሸፍ።

j) የሌሎች ተጠቃሚዎችን ኢ-ሜይል ያለፈቃድ መደለዝ-Deleting፣ አስመስሎ መሥራት-forging፣ ለውጥ አድርጎ ማሻሻል-modifying ወይም ማንበብ-reading ወይም ቅጂ-ኮፒ ማድረግ-copying ወይም ለማድረግ መሞከር።

k) ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና/ወይም በእርሱ(ሷ) ተወካይ ሳይፈቀድ ማንበብ፣ መደለዝ፣ መገልበጥ፣ ማስተላለፍ፣ ማተም፣ ማጋራት፣ ወይም በሌሎች ተጠቃሚዎች ዳታ ላይ ለውጥ ማድረግ።

l) የአንድን ሰው የግል የ MCPS ኢ-ሜይል አድራሻ፣ አካውንት፣ ወይም ይለፍ ቃል/password ሌሎች እንዲጠቀሙ መፍቀድ።

m) የአንድን ሰው የግል የ MCPS አውታረመረብ አካውንት-network account፣ የአውታረመረብ ፋይሎች-network folders፣ ወይም ይለፍ ቃል-password ሌሎች እንዲጠቀሙ መፍቀድ።

n) የንግድ ማስታወቂያዎችን፣ chain letters፣ ወይም ትምህርታዊ ያልሆኑ መጫወቻዎችን-noneducational games በ MCPS ሲስተሞች መጠቀም።

o) የባለቤትነት መብት ያላቸውን-copyrighted ቁሳቁሶች/ማቴሪያሎች እና ሶፍትዌር ያለፈቃድ መገልበጥ ወይም ማስተላለፍ።

p) ሳይፈቀድ ተለይተው የሚታወቁ የግል መረጃዎችን በኢንተርኔት ፖስት ማድረግ ወይም በኤሌክትሮኒክ መገልገያ አማካይነት ማሠራጨት ወይም ስለ ተማሪዎች ወይም ሠራተኞች፣ የ MCPS መሣሪያዎችን ወይም ሪሶርሶችን በመጠቀም ሀሰተኛ መረጃዎችን ፖስት ማድረግ።

q) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) አውታረመረቦች-networks ወይም የኮምፒውተር ሲስተሞች ለግል ጥቅም ወይም ህገወጥ ለሆኑ ተግባሮች መጠቀም።

9. ተጠቃሚዎች በጠቅላላ በዝቅተኛ የእድሜ ክልል ስለሚገኙ ልጆች-minors ያልተፈቀደ የግል መረጃ/ኢንፎርሜሽን መግለጽ፣ መጠቀም፣ እና ማሠራጨት ላይ እያወቁ መሣተፍ የተከለከለ ነው።

10. በኦንላይን ስለሚደረጉ የግንኙነቶች ስነምግባር ከሌሎች ግለሰቦች ጋር የሚደረጉ መግባባቶችን ጭምር በማህበራዊ የመገናኛ አውታሮች እና በውይይት ክፍሎች-chat rooms፣ በኤሌክትሮኒክ መጠቀሚያ ማስፈራራትና ዛቻ ግንዛቤ መፍጠር እና ምላሽ ስለመስጠት ተማሪዎች መማር አለባቸው።

11. የ MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞችን የሚገለገል ማንኛውም ተጠቃሚ በቴክኖሎጂ መከላከያ-መጠበቂያ ዘዴ ያልተጣራ በከፊል አግባብ ያልሆነ የተለየ አይነት ማቴሪያል ካገኘ(ች) ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ደንብ እና ሥርአት እንዲከተል/እንድትከተል ይጠበቃል Manual of MCPS Computer Systems Security Procedures በ MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

V. አለመታዘዝ-NONCOMPLIANCE

A. በዚህ ደንብ ላይ የተገለጹትን ሥርአቶች እና ወጎችን አለማክበር-አለመታዘዝ የዲስፕሊን እርምጃ ለማስወሰድ በቂ ምክንያት ነው።

1. በሠራተኛ ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ ሊያካትት የሚችለው፡- ኮንፈረንስ፣ ማስጠንቀቂያ፣ የግሣጼ ደብዳቤ፣ የተለዩ ጥቅሞችን ማጣት፣ ያለክፍያ መታገድ፣ ከደረጃ ዝቅ መደረግ፣ ከሥራ ስንብት፣ እና/ወይም የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስከትል ይችላል።

2. በተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ፡- በዚህ የተገደበ ባይሆንም፣ ወላጆችን/ሞግዚቶችን በስልክ መጥራት፣ የግል ጥቅሞችን መከልከል፣ የጠፋ-የተበላሸን ነገር መመለስ፣ መታገድ፣ እና/ወይም ማስወጣት፣ እና/ወይም በወንጀል ተጠያቂነት። (የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS Regulation JFA-RA ይመልከቱ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች-Student Rights and Responsibilities እና የትምህርት ቤት ስነ-ስርአት ፖሊሲዎች-school discipline policies)

3. በሌሎች ላይ የሚወሰድ የዲስፕሊን እርምጃ ልዩ መብት/ጥቅምን ማጣት እና/ወይም የወንጀል ተጠያቂነትን ያካትታል።

B. ማንኛውም የ MCPS ኮምፒውተር ሲስተሞች ተጠቃሚ የሚያስጠረጥሩ ወይም ተገቢ ያልሆነ የዳታ አጠቃቀም፣ የኮምፒውተር ሲስተም ህገ-ወጥ አጠቃቀም፣ ወይም ለደህንነት ጥሰት የሚያበቁ ነገሮችን ሪፖርት ማድረግ አለበ(ባ)ት። ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረጉ ተጠቃሚዎች ለርእሰመምህር ወይም ለተወካይ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኃላፊነት ያለው/ያላት ሰው እንዲያውቅ-እንድታውቅ ማድረግ አለባቸው። በትምህርት ቤት ያልተመሠረቱ ተጠቃሚዎች ለቅርብ ተቆጣጣሪያቸው እና ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት እና/ወይም ለተወካይ ማሳወቅ አለባቸው። ከባድ የህግ ጥሰቶች፣ በ--እንደተገለጹት አይነትየሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የኮምፒውተር ሲስተሞች ደህንነት የአሰራር መምሪያ መጽሐፍ-Manual of MCPS Computer Systems Security Procedures፣ እንደዚሁ ለ OCTO ሪፖርት መደረግ አለበት።

**ስለ ደንቡ ታሪክ፦** ኦገስት 22/1995 አዲስ ደንብ፣ ዲሴምበር 13/1999 ተከልሷል፣ ጁን 1/2000 የቢሮዎቹ ስያሜዎች ተሻሻሉ፣ ጁን 10/2002 ክለሳ ተደርጓል፣ ሜይ 23/2007 ተከልሷል፣ ጁላይ 27/2012 ተሻሽሏል።.